የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

# የኢፌዴሪ ረቂቅ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ላይ

# ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተሰጠ

# አጠቃላይ እና ዝርዝር አስተያየት

## መግቢያ

በፍትሕ ሚኒስቴር የተቋቋመው የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች የስራ ቡድን በየካቲት ወር 2016 ዓ.ም. ረቂቅ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ሰነድ አዘጋጅቶ ለፍትሕ ሚኒስቴር በይፋ እንዳስረከበ ይታወሳል። ከየካቲት ወር 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በዚህ ረቂቅ ፖሊሲ ላይ የተለያዩ የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ፖሊሲው ከተሰበሰበው ግብአት አንጻር የመመርመርና የማረጋገጥ ስራ (validation process) መጀመሩ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ/ኮሚሽኑ) ረቂቅ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ሰነድን ተመልክቶ የሚከተሉትን ትንታኔዎችና ምክረ ሃሳቦች አቅርቧል፡፡ ይህ አስተያየትና ምክረ ሃሳብ የተሰጠው በኢሰመኮ የማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 210/1992 አንቀጽ 6 (2) እና (5) ስር ለኮሚሽኑ በተሰጠው *"በመንግሥት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች በሕገ መንግሥት ከተረጋገጡ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን የማረጋገጥ"* ተግባርና ኃላፊነት መሠረት ነው፡፡ የመነሻ ሰነዱን ጠንካራ ጎኖች፣ አንኳር አስተያየቶችን እና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ አጠቃላይ አስተያየት ከሚያቀርበው የመጀመሪያ ክፍል በኋላ የኮሚሽኑ ምክረ ሃሳብ ዝርዝር ትንታኔ ይከተላል፡፡

## ጠቅላላ አስተያየት

1. *በረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱ ላይ የሚደረጉ ውይይቶች ግልጽነት እና አካታችነትን በተመለከተ*

የረቂቅ ፖሊሲውን ይዘት ለማህበረሰቡ አቅርቦ በማረጋገጥ ሂደት ወቅት ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍ የሚደረገው ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም፣ በሂደቱ ላይ የግልፅነትና አካታችነት መርሆዎች በበቂ ሁኔታ አለመተግበራቸው አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ሰነዱን ለውይይት ተሳታፊዎች ቀደም ብሎ አለመስጠቱና የሲቪክ ማህበራት ተወካዮች ከአባሎቻቸው ጋር ለመማከር የሚያስችል በቂ ጊዜ አለመስጠቱ ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዳያደርጉ ምክንያት ሆኗል። ለውጤታማ አስተዳደር እና ለፖሊሲ ውሳኔዎች ሕጋዊነት የግልጽነት እና አካታችነት መርሆችን ማስከበር ወሳኝ እንደመሆኑ መንግስት ረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱን ለሕዝብ እንዲያካፍልና የሚቀርቡለትን አስተያየቶች ከዚህም በኋላ ጊዜ ሰጥቶ እንዲቀበልና እንዲያጤን እንመክራለን።

2. *የሽግግር ፍትህ መነሻ እና አስፈላጊነትን በተመለከተ*

ረቂቅ ሰነዱ የሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት እና መነሻ መሠረት ያደረገው ግጭቶች እና ለግጭት ምክንያት የሆኑ ትርክቶች ላይ ነው። እነዚህም በአብዛኛው በተፈጸሙ (commission) የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ያተኮረ ነው። ነገር ግን ለእነዚህ ትርክቶች እና ግጭቶች መነሻ የሆኑ መዋቅራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መብቶች ጉዳዮች (ለምሳሌ እንደ መሬት እና የተፈጥሮ ሀብቶች ባለይዞታነትን ማሳጣትን፣ ልማዳዊ አጠቃቀምን ማሳጣት የመሰሉ) እንዲሁም የመልማት እና ከሌላዉ ማህበረሰብ እኩል ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን በማጣት በአንጻራዊነት ያላደጉ (marginalised) እና የፖለቲካው ዳርቻ (periphery) ላይ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ጉዳይን በሚመለከት እና ማህበራዊ ፍትህን ለማረጋገጥ ጭምር ያለመ መሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይመከራል ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚነሱ የእርስ በእርስ ግጭቶች ከመሬት እና የተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም የብሄር ማንነትና ወሰን አስተዳደር ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው። ለምሳሌ በአፋር እና በሱማሌ፣ ወልቃይት እና ራያን በተመለከተ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች፣ በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች፣ በቤንሻንጉል እና ቢጋምቤላ፣ በኦሮሚያና አጎራባች ክልሎች እንዲሁም በደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ በርካታ ግጭቶች ከመሬት ይዞታ፣ ከብሄር/ብሄረሰብ ማንነትና የወሰን አስተዳደር ጋር በተያያዘ ለዘርፈ ብዙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምክንያት በመሆኑ፤ ይህን አውድ እና እነዚህን ጥሰቶች ያስከተሉ መዋቅራዊ ማነቆችን መፍታትንም ጭምር እንደ መነሻ እና ለሽግግር ፍትህ አስፈላጊነት ታሳቢ አድርጎ ማስቀመጥ ይመከራል።

*3. አስገድዶ መሰወርና የጠፉ ሰዎች ጉዳይ*

በጦርነት ዐውድና በግጭት ጊዜ የአስገድዶ መሰወርና የጠፉ ሰዎች ሁኔታ በብዛት ያጋጥማል። የኢሰመኮ ክትትልና ምርመራም ይህንን ሁኔታ ያሳያል። ነገር ግን ረቂቅ ፖሊሲው በዚህ ጉዳይ ላይ የጠቀሰው ነገር ስለሌለ፤ የአስገድዶ መሰወር ሰላባ ስለሆኑና ስለጠፉ ሰዎች ጉዳይ በሽግግር ፍትሕ ማዕቀፍ እንደሚጣራ በረቂቅ ሰነዱ ላይ በግልጽ ቢቀመጥ ይመከራል ፡፡

*4. የበጀት ነጻነትን በተመለከተ*

በፖሊሲው አማካይነት እንደሚቋቋሙ የሚጠበቁት የልዩ ዐቃቤ ሕግ፣ የልዩ ፍርድ ቤት፣ የእውነት አፈላላጊ እና የተቋማዊ ማሻሻያ ተቋማት ነጻ እና ገለልተኛ እንዲሆኑ ለማስቻል በቂ በጀት የሚመደብላቸው ብሎም የተመደበውን በጀት የማስተዳደር ነጻነት እንዲኖራቸው እንደሚደረግ በተለያዩ የፖሊሲው ክፍሎች ተመላክቷል። ከዚህ በተጨማሪነት፣ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያከናውን ከሚጠበቀው መደበኛ የሃብት ማፈላለግ ተግባር በተጨማሪ ተቋማቱ የተሟላ የሽግግር ፍትሕ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችሉ ራሳቸውን ችለውና ነጻነታቸውንና ተልዕኳቸውን በማይቃረን መንገድ የገንዘብ እና የዓይነት ድጋፍ ከልዩ ልዩ አጋር ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ አካላት ለማሰባሰብ የሚያስችል ነጻነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይመከራል።

የኢትዮጵያ
ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN
RIGHTS COMMISSION

## ዝርዝር አስተያየት

| # | ክፍል/አንቀጽ | ማብራርያ | አስተያየት |
|---|---|---|---|
| 1. | "የቃላት እና የሀረጋት ፍቺ" በሚለው ስር በተራ ቁጥር 9 ስር የተቀመጠው ትርጉም | "ተጎጂ" የሚለውን ቃል ከመጠነ ሰፊ ወይም ተከታታይነት ያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር ብቻ አያይዞ መተርጎም የሌሎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎችን ከሽግግር ፍትህ ሥርአት ፍትህ ማግኘት እንዳይችሉ ወይም ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚያደርግ ትርጉም ሊጋብዝ ይችላል። | "ተጎጂ" የሚለውን ቃል የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች፣ የሰብአዊነት እና የዓለም አቀፍ የወንጀል ጥሰቶች፤ በመንግስትም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የተፈጸሙ ጥሰቶችን ጨምሮ፤ በሰላምም ሆነ በጦርነት ሰዓት ለደረሱ የመብት ጥሰቶች በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ተጎጂ የሆኑ ሰዎችን ሁሉ በሚያካትት መልኩ ትርጉም ቢሰጠው ይመከራል። |
| 2. | ልዩ ትኩረት የሚሹ የማሕበረሰብ ክፍሎች | ልዩ ትኩረት የሚሹ የማብረሰብ አባላትን በሚመለከት በፖሊሲው ውስጥ በተለያዩ ክፍሎች ወጥነት የሌላቸው ድንጋጌዎች ተካትተዋል። እነዚህን የማብረሰብ አባላት የሚዘረዝር አንድ ጠቅላላ ድንጋጌ ማስቀመጥ ሁሉም ልዩ ትኩረት የሚሹ ሰዎች በሁሉም አሰራሮች ውስጥ ከግምት ውስጥ እንዲገቡ እና በሽግግር ፍትህ ሂደቶች ውስጥ እንዲካተቱ የተሻለ ማረጋገጫ ይሆናል። | "የቃላትና የሃረጋት ፍቺ" በሚለው ክፍል ውስጥ ልዩ ትኩረት የሚሹ የማብረሰብ አባላትን ፍቺ ማካተት ይመከራል።<br><br>ይህም በሁሉም የሽግግር ፍትሕ ሂደቶች ውስጥ ሁሉንም ትኩረት የሚሹ የማብረሰብ አባላት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ አንድ ዓይነትና ግልጽ የሆነ ድንጋጌ እንዲኖር ያደርጋል። |
| በክፍል አንድ ፥ "ፖሊሲው የሚመራባቸው መርሖዎች" ስር | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | በተራ ቁ. 1.5.7. ***አካታችነትና አሳታፊነት፡-*** *የሽግግር ፍትህ ሂደት በፖለቲካ አመለካከት፣ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ ወይም በሌላ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ልዩነትን ሳያስተናግድ፣ ማንኛውንም አድሏዊ መስፈርት እና አመለካከትን በማስወገድ ግልጽ፣ ሁሉን-አቀፍ፣ አካታች፣ በሀገሪቱ ያለውን ብዝሀነት በሚያንፀባርቅ እና ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በሚያሳትፍ መንገድ ይተገበራል፤* የሚለው | ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሃይማኖት እና የአካል ጉዳት ልዩነትና አድልዎ ሊደረግባቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ስለሆኑ በግልጽ መጥቀሱ ይመከራል፡፡ | ከተዘረዘሩትን ሁኔታዎቸ በተጨማሪ ሃይማኖት እና የአካል ጉዳትን በሚያካትት መልኩ ማሻሻያ ቢደረግበት ይመከራል፡፡ |
| 4. | በተራ ቁ. 1.5.9. *ልዩ ትኩረት የሚሹ የማብረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ፡ የሽግግር ፍትህ ሂደት ትግበራ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የመብት ጥሰት ሰለባዎች፣ የተፈናቃዮች፣ የሴቶች፣ የህጻናት፣ የአረጋውያን፣ እና የአካል እና የአዕምሮ ጉዳት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ፍላጎት እና ምልከታን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እንዲሁም በሂደቱ ላይ ያላቸውን ባለቤትነት የሚያረጋገጥ ይሆናል፤* የሚለው | “ተፈናቃዮች” የሚለው ቃል “የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች” የሚመለከት ስለሆነ በጠቅላላው ሰነድ በዚሁ መልኩ ቢስተካከል ተገቢ ነው፡፡ | “ተፈናቃዮች” የሚለውን ቃል በ “ሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች” በሚል ቢተካ እና በሰነዱ ሌሎች ቦታዎችም ላይ በተመሳሳይ ቢስተካከል ይመከራል። |
| በክፍል ሁለት ፥ 2.1.1. ስር ምርመራ እና ክስ የሚከናወንባቸው ወንጀሎችን በተመለከተ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | በ 2ኛው ነጥብ ላይ *በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በተመለከተ ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ አዲስ የሕግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፤* የሚለው | የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች በሚመለከት ለወደፊቱ ሕግ እንዲወጣ መሆኑ ትክክል ሲሆን፤ ከዚህ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎችን በሚመለከት ግን በዓለም አቀፍ ሕግ መሰረት ተጠያቂነት የሚረጋገጥበትን መንገድ ማመላከት ያስፈልጋል፡፡ | የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎች በዓለምአቀፍ የልማዳዊ ሕግ መሰረት በመክሰስ ወይም *jus cogens* ተብለው የሚቆጠሩትን ደንቦች መሰረት በማድረግ ተጠያቂነት የሚረጋገጥ መሆኑን በፖሊሲው መጥቀስ ይመከራል፡፡ |
| በክፍል ሁለት ፥ 2.1.2. ስር ምርመራ የሚከናወንባቸው እና ክስ የሚመሠረትባቸው አጥፊዎችን አስመልክቶ ተግባራዊ የሚሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎች እና ስልቶችን በተመለከተ | | | |
| 6. | በ5ኛው ነጥብ– *“በመደበኛ የምርመራ ሂደት ሊደረስበት የማይችል ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያለው አጥፊ የሚገኝበትን ቦታ ለጠቆመ ወይም አጥፊው በጉልሕ የሰብአዊ መብት ጥሰት/ከባድ ወንጀል መሳተፉን የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ላቀረበ ሰው የማበረታቻ ድጋፍ ወይም ሽልማት የሚሰጥበት ሥርዓት ይመቻቻል፤ ”* የሚለው | ከማበረታቻ ድጋፍ ወይም ሽልማት በተጨማሪ ይህንን በማድረጋቸው ሊደርስባቸው ከሚችል አደጋ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚያስችል ሥርዓት እንደሚዘረጋም ማመላከት ተገቢ ነው። | በማብራሪያው መሠረት ማስተካከል ይመከራል፡፡ |
| በክፍል ሁለት ፥ 2.3.1. ለምህረት ብቁ የማያደርጉ ሁኔታዎችን በተመለከተ፡ | | | |
| 7. | በዚህ ፖሊሲ ‘ለወንጀል ተጠያቂነት’ ዓላማ ‘ጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች’ እና ‘ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎችን’ በተመለከተ በተሰጠው ትርጉም መሰረት – ‘በጉልህ የሰብዓዊ *መብቶች ጥሰቶች ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች’ የምህረት ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡* የሚለው | ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶችና የሰብአዊነት ሕጎች ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈፀሙ አጥፊዎች ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይኖርባቸው ደንግገዋል።<br><br>ሆኖም በፖሊሲ ሰነዱ ላይ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎችን ብቻ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆኑና በምህረት ተጠቃሚ እንደማይሆኑ ስለሚገልጽ ከዓለም አቀፍ ሕጉ ጋር የሚቃረን በመሆኑ ቢስተካከል ይመከራል፡፡ | በማንኛውም ደረጃ ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ወይንም ከባድ ወንጀል ላይ የተሳተፉ ሰዎችን ተጠያቂ ማድረግ ስለሚገባ ከፍተኛ ደረጃ ተሳትፎ የሌላቸውንም አጥፊዎች የምህረት ተጠቃሚ እንደማይሆኑ በፖሊሲው ቢጠቀስ ይመከራል። |